# የትምህርት ፖሊሲው ስኬትና ምጣኔ ሀብታዊው ዕድገታችን

**ዮናስ 8/10/11**

ጀርመን ሁለት ሦስተኛው የሚሆነው ምጣኔ ሀብቷ እና ዋና ንብረቷ በጦርነት ምክንያት ከወደመና ከፈራረሰ በኋላ እስከ 20 ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ መልሳ የገነባችው በተዓምር ሳይሆን በመደራጀት፣ በዲሲፕሊንና በፍላጎት በመመራት ነው።´ ይህን ሀሳብ የወሰድኩት ከፍኖተ ነፃነት ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም እትም ነው፡፡

ፀሀፊውም ዶክተር ፍቃዱ በቀለ የተባሉ ግለሰብ ናቸው። ዶክተር ፍቃዱ ምን መደረግ አለበት? ሲሉ ባቀረቡት በዚህ ጽሁፍ ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት (ለእኔ እንደገባኝ) ሀገራችንን ከድህነት ለማውጣት ምን መደረግ እንዳለበት ገዥውን ሥርዓት የመምከር ዓይነት ነው።

ዶክተር ፍቃዱ ገዥው ሥርዓት ያደረገውንም ያላደረገውንም ሳይለዩ እርስ በርሱ በማጣረስ ሊበራላዊ፣ አምባገነናዊና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ርዕዮቶችን ደበላልቀው ያቀረቡት ሀሳብ ቅዠት ከመሆኑ ባሻገር የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታና ማህበራዊ ፖለቲካዊ እሴቶች ያላገናዘበ ተራ ነቢብ ነው።

በሌላ በኩል በዚሁ እትም ላይ የተሳከረው የምጣኔ ሀብት ፖሊሲና ውጤቶቹ ሲል ነብዩ ኃይሉ የተባሉ ፀሐፊ ያስነበቡን ሌላው ጽሁፍ ነው፡፡ የኢህአዴግን የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ የተበላሸ ነው ሲሉም የበለጠ ኮንኖታል።

የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም በኢትዮጵያ በተካሄደበት ወቅት ጎይቶም የተባሉ ግለሰብ የኢትዮጵያን የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ የማያዋጣ ነው ሲሉ የተቹበትን ፅሁፍ አስነብበውናል። ያለ ምንም መረጃና ማስረጃ ውኃ በማይቋጥር ምክንያቶች የታጀሉት እነዚህ ጽሁፎች የሌሎችን ጉድፍ ከማየታቸው አስቀድመው በአንድ የህትመት ውጤት ላይ እርስ በርሱ የተሳከረና አንዳንዴም እንደ ዶክተር ፍቃዱ ከራሳቸው ሀሳብም ጋር የተጣሉ ስለመሆናቸው መገንዘብ የነበረባቸው ይመስለኛል። ዳሩ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣና ባለቤቷ አንድነትም በተሳከረ ጉዳይ ላይ እየተንገዳገዱ በመሆናቸው ኤዲተሮቹ ይህን ለማጤን የሚችሉበት እድል ያለ አይመስለኝም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለዛሬው መጣጥፌ መነሻ የሆነኝ ሌላው ዐቢይ ምክንያት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎችን እና የሥራ እድልን በተመለከተ ከሰሞኑ ይሰጡ የነበሩ አስተያየቶች ናቸው። በተለይም አዲስ ጉዳይ በተባለው መጽሄት ላይ ዐቢይ ሆነው የሰፈሩት አስተያየቶች።

|ወጣቶች በምርቃታቸው ወቅት ሥራ እንፈጥራለን የሚለው አስተሳሰብ ከእነሱ አንደበት መሰማቱ አንድ ትልቅ እድገት ነው።´ የትምህርት ሚኒስትሩ ከሰሞኑ ጉዳዩን አስመልክተው ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ነበር።

ወላጆችም ልጄ ተቀጥሮ ይሰራል ከማለት እና የአጭር ጊዜ ህልም ከማለም ይልቅ ከተቋማቱ ልጄ እውቀት፣ ክህሎት የአመለካከት ለውጥ ታጥቆ በመውጣት ትልቅ ኩባንያ ኖሮት ቢሊነየር እንዲሆን እፈልጋለሁ ማለት አለባቸው። ወጣት ምሩቃን በመንግሥት ተቋማት የመቀጠር ሥነ ልቦና ሳይሆን የመቅጠር ሥነ ልቦና ይዘው መውጣት ይገባቸዋልና።

የወጣቶቹን በኮብል ስቶን ሥራ መሰማራት በዋናነት ካየነው ከፖሊሲ ውድቀት አንፃር ሳይሆን በቀጣይ ለሚያስቡት ትልቅ ደረጃ መሠረት የሚጥሉበትን ገንዘብ የሚያፈሩበት የሥራ መስክ ከመሆኑ አንፃር መመልከት ያስፈልጋል።

አዲስ ጉዳይ መጽሄትም |ለምን እንማራለን´ በሚል ርዕስ ባወጣው ጽሁፉና ዐቢይ ጉዳዩ ተምሮ ድንጋይ መጥረብን በአንድ አቅጣጫ ብቻ በማየትና ከመንግሥት የመቅጠርና ከምጣኔ ሀብቱ የመሸከም አቅም በላይ የሆነ የተማረ ኃይል በሚል ቢያብጠለጥለውም |ሥራ አለ ሥራ የለም´ በሚለው ተከታዩ እትሙ ደግሞ ፀሃፊው ከራሱ እይታ በመውጣት ያነጋገራቸው በሁለት ጽንፍ የሚገኙ ግለሰቦች |ለምን እንማራለን´ በሚለው ርዕስ ላይ ያሰፈረውን አስተሳሰብ አስቀይሮታል።

ይኸውም የሥራ ባህላችን፣ የጠባቂነት መንፈሳችን እና በይሉኝታ የተጠቃን መሆናችን ሥራ ለመፍጠርና በተገኘው መስክ ተሰማርተን ለመለወጥ ሊኖረን የሚገባውን መንፈስ በተመለከተ ያነጋገራቸውን ግለሰቦችና ከትንሽ ተነስተው ዛሬ አንቱ የተባሉ የሀገራችንን ኢንቨስተሮች ለአብነት በማንሳት አብራርቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሀገራችን የተገኙ አጋጣሚዎችን የሚንቁ ግለሰቦች በአውሮፓ፣ በምድረ አሜሪካና የዐረብ አገራት ፈረስ ሲያጥቡ፣ አስፓልት ሲጠርጉና መፀዳጃ ቦታዎች ላይ ሁሉ መስራታቸው ፀሀይ የሞቀው እውነታ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ባህላችንና አመለካከታችን ከፖሊሲው በላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው የጠቆመው መጽሄት፣ "ምን ነክቶኝ የወረደ ሥራ እሰራለሁ" የሚሉ ወጣቶች ዛሬ በየካፌው ወንበር ሲያሞቁ መዋላቸው እየታየ በመሆኑ ከትምህርት ፖሊሲው ጋር መያያዝ እንደሌለበትም አንድ የውጭ ዜጋን ምልከታና አስተያየት መሠረት በማድረግ አብራርቷል።

ከኮብል ስቶን ጠረባ፣ ከዶሮ ልማትና መሰል የጥቃቅን እና አነስተኛ የሥራ ዘርፎች ጋር ተያይዞ በየአጋጣሚውና በተለይም በግል ፕሬሶች አካባቢ ዋነኛ አጀንዳ የመሆኑ ምክንያት ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያቀረባቸው ፕሮግራሞች እንደሆኑ ይገለፃል። በእኔ አስተያየት መሠረታዊው ምክንያት

የፖሊሲ ሳይሆን የኢቴቪ ጋዜጠኞች የአቀራረብና ግባቸውን ያለማወቅ ጉዳይ ይመስለኛል። በቃ ከፕሮግራሞቹ እኔም ያስተዋልኩት ነገር የተማረ ወጣት የመጨረሻ መድረሻና ብቸኛ አማራጭ ኮብልስቶን እንደሆነ የሚመሰል ዓይነት አቀራረብ ነው። ነገሩ ግን ያ አይደለም። መጀመሪያ መመልከት ያለብን የትምህርት ፖሊሲውን እንጂ የኢቴቪ ፕሮግራምን መሆን የለበትም። ከኢቴቪ ተነስተን የትምህርት ፖሊሲውን ማብጠልጠል ምክንያታዊ ሊያደርገን አይችልም። ከፖሊሲው ተነስተን ኢቴቪን መገምገምና ተሳስተሀ አታሳስተን ማለት ግን ቀናነትና ኃላፊነት የሚሰማው ሰው አስተሳሰብ ነው። ስለኮብልስቶን ለማውሳት የፖሊሲውን ዓላማ መጀመሪያ እንመልከት።

የሀገራችን የትምህርትና ሥልጠና ዓላማ የተያዘውን የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ እድገትና ምጣኔ ሀብቱ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራትና ለማብቃት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ፤ ከምጣኔ ሀብቱ ጋር ተጣጥሞ እና በተመጋጋቢነት የሚሄድ እንጂ አንዱ ለብቻው ተነጥሎ የሚታይበት ሥርዓት አይደለም - ቢፈለግም እንኳ ስለማይሆን። የፖሊሲው ተልዕኮም የልማትና የዴሞክራሲ ፕሮግራሞችን ማሳካት ነው። በዚህ ተልዕኮ መሠረት ወጣቶች በብቃት ሰልጥነው በግልም ሆነ በመንግሥት በየትኛውም ዘርፍ ተወዳዳሪ እና ስኬታማ የሚሆኑበትን ዕድል መፍጠር ነው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ዋነኛ ዓላማ።

በዚህ መሠረት ኢቴቪ ስለተናገረ ኮብል ስቶንን ብቻ ይዘን ሳይሆን በማናቸውም ዘርፍ ወጣቱ ተወዳዳሪና ብቁ ሆኖ እንዲወጣ ከተደረገ ሌላው በሂደት የሚመጣና እንደኮብል ስቶን ዓይነቶቹ ለተማረው የሰው ኃይል እንደመነሻና መሠረት ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ግምት መውሰድ ያስፈልጋል።

ሌላው ከተማሪዎች የምረቃ በዓል ጋር ተያይዞና ከኢቴቪ ፕሮግራሞች ጋር ተያይዞ ሲነሳ የነበረው የትምህርት ጥራት ነው፡፡ ይኸውም የሚመረቁ ተማሪዎችን ብዛት ብቻ በመመልከት የት ሊገቡ ነው? ከሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ በመነሳት እንደ ድሮው ይሁን ዓይነት ምኞት የሚንፀባረቅበት አስተያየት፡፡

ሆኖም ግን የትምህርት ጥራት ከሥራ ዕድል ለዚያውም ከቁጥር ጋር ብቻ ተያይዞ የሚለካ ሳይሆን ጉዳዩ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በዋናነት ግን የትምህርት ጥራትም ቢሆን መታየት ያለበትና መነሻው ፖሊሲው መሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ፖሊሲው ጥራቱን የሚመለከተው ከእድገት ደረጃችን ከኢንዱስትሪዎቻችን ፍላጎት፣ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን በአጠቃላይ ከምጣኔ ሀብታችን እንቅስቃሴ ጋር ተጣጥሞ በየጊዜው እየተፈተሸና እየታደሰ እንዲሄድ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህም ጥራት በአንድ አዳር የሚታይ ጉዳይ ሳይሆን እንደ ምጣኔ ሀብቱ አብሮ በሂደት እየተገነባ የሚመጣ ጉዳይ ነው፡፡ በ1998 ዓ.ም ቁልፍ በሆኑ የትምህርት ግብዓቶችና የትምህርት ይዘቶች ላይ ጥራትን ለማምጣት የተቀረፁትን ስድስት

ፕሮግራሞች እዚህ ላይ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ የትምህርት አመራር፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ የመምህራን ደረጃ፣ ትምህርት በቴክኖሎጂ፣ ትምህርትን በሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት የሚሉት ፕሮግራሞች በሌሎችም ተመሣሣይ ሀገሮች ውጤት የተገኘባቸውና የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ በሥራ ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

ይህን ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር አያይዘን ስንመለከተው በቴክኖሎጂው ዘርፍ አንድ ተማሪ ቢያንስ አንድ ሴሚስተር ኢንዱስትሪ ውስጥ ገብቶ መሰልጠን እንዳለበት ያስገድዳል፡፡ ያን ያላደረገ ተማሪ አይመረቅም፡፡ ሲመረቅም ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያለውና በተግባር ትምህርት ወቅት ያገኘውን እውቀት ያገናዘበ የመመረቂያ ጽሁፍ ጽፎ እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡ በክለሣ ድርሳናት ላይ ብቻ ያተኮረና በተግባር ያልተደገፈ መመረቂያ ጽሁፍ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላውና ፖሊሲው ስለትምህርት ጥራትና ተገቢነት እንዲሁም ሥራ ፈጣሪነት ትክክለኛውን መንገድ ይዟል ሊያስብለን የሚችለው ጉዳይ ከታችኛው የትምህርት እርከን ጀምሮ እየተሰራ የሚገኘው ሥራ ነው፡፡

ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት በማሻሻል ህፃናት ለቴክኖሎጅና ሣይንስ ቅርብ እንዲሆኑ፣ ደፋርና የሚሞክሩ፣ ይህን አትንካ ይህን ንካ ከሚል ባህል ወጥተው በድፍረት እየሞከሩና ሥራ ፈጣሪ የሚሆኑበትን መንገድ እያመቻቸ ነው፡፡ የ70/30 ጉዳይም መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለሆነም ትምህርትን የሁሉም ሀብት ማድረግ የትምህርት ፖሊሲው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የህገ መንግሥትም ጉዳይ ነው። የትምህርት ማስፋፋትን ጉዳይ ተንተርሶ ከምጣኔ ሀብቱ ጋር ያልተጣጣመና ተገቢነት የሌለው ነው ማለት ጫፍ ይዞ ከፖሊሲ ውጭ የሆኑ ጉዳዮችንና በተግባር ላይ ካሉ ስኬቶች ባሻገር በመመልከት ለተራ ፖለቲካዊ ፍጆታ ማዋል ኃላፊነት ከጎደለው ዜጋ የሚመነጭ እንጂ በተግባር በመሬት ላይ ያለው ሁሉ ከላይ የተጠቀሰው ነው፡፡

ለማናቸውም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ተከታታይነት ያለው ዕድገት ያስመዘገበችው፤ ዕድገቷም በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የተረጋገጠላት በዘረጋችው የግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲዋና የአፈፃፀም ስልቷ መሆኑን በዚያው ‹በምትወዱት› ኢቴቪ እያያችሁ ይመስለኛል። ሞዴል እና ግንባር ቀደም ከሆኑ አርሶ አደሮች የተገኙ ምርጥ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ሌሎቹም አርሶ አደሮች የማስፋቱ ጥረት ባለፉት ዓመታት በርካታ ሚሊዬነሮችን እንዳፈራው ሁሉ፤ ከክልል ክልል፣ ከዞን ዞን፣ ከወረዳ ወረዳ፣ ከቀበሌ ቀበሌ እያለ እስከ ታችኛው ጎጥ ድረስ የነበረው የግብርና ሥራና የማበረታቻው ሽልማቶች ሁሉ ያመጡትን ውጤትም እየመረረንም ቢሆን ልንውጠው የሚገባን ሌላው እውነት ነው።

ሌላው እነዚህ ኃይሎች የተሳከሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥልንና እርስ በርስ እንኳን የማይታያዩ የጋሪ ፈረሶች ስለመሆናቸው መገለጫ የሚሆነን በጽሁፌ መግቢያ ላይ የጠቀስኩት የፍኖተ ነፃነት

አምደኛው ዶክተር ፍቃዱ ስለጀርመን ዕድገትና የመደራጀትን ጥቀም የገለፁበት አስተያየት ነው። እሳቸው ካለመደራጀት እና ካለ ዲስፕሊን ማደግ አይቻልም ሲሉ ጀርመንን ምሣሌ ያደርጋሉ፤ አጋሮቻቸው ደግሞ መደራጀትን ይነቅፋሉ። ታድያ የተሳከረው ማን ነው?

ለወትሮው ፈረንጅ አምላኪና የየኤምባሲው ደጅ ጠኚ መሆናቸውን የምናውቅላቸው የፍኖተ ነፃነት ባለቤት የሆኑት አንድነቶችና አጋሮቻቸው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም በኢትዮጵያ በተካሄደበት ወቅት ለምን ተካሄደ ብለው ፈረንጆቹን  መነትነታቸውን እናስታውሳለን። የተመኙት አመጽና ነውጥ ይሳካ ይሆናል ብለው በሚያልሙበት በዚያ ወቅት ፈረንጆቹ ስለኢትዮጵያ እድገት እና ለውጥ በተለይም በግብርናው መስክ ስለተገኙት አመርቂ ውጤቶች መመስከራቸው፣ ይህንኑም ለሀገሪቱና ለመሪዋ አድናቆታቸውን መግለጻቸው ተስፋቸውን ያሰለለባቸው የፍኖተ ነፃነቱ  የወቅቱ ተዋናይ ያለአንድ ማስረጃና ማሣያ ፈረንጆቹን በመወትወት ለመንግሥት ያላቸውን ጥላቻ አሳይተውናል።

ፈረንጆቹ ይህን ታላቅ ጉባኤ በኢትዮጵያ ለማድረግ ሲነሱ ምን መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልገው ነው? ‛ፈረንጆቹ የአቶ መለስን አምባገነን መንግሥት እንደሚደግፉ በኢህአዴግ የብረት ጫማ ከላይ ለሚረገጠው ደሀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመናገር ነው ብዬ እገምታለሁ።′ የሚሉት ‛ፀሀፊ′ ፈረንጆቹ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያልተቃቡትን ደም እያወራረዱ እንደሆነ የሚመስል የጅል ሀሳብ ያቀርባሉ።

በዋጋ ንረት ከዓለም አንደኛ ነን ሲሉ ያጫወቱን  አቶ ኀይቶም  የሀሰት የምጣኔ ሀብት መረጃዎችን ደግሞ ማን እንደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይፈበርካል?  ሲሉ በመጠየቅ ነበር የቅናታቸውን ውጤት የደመደሙልን።

አቶ ኀይቶም ፈረንጆቹን ላብጠለጠሉበት የፍኖተ ነፃነትና አንድነት ፈረንጅ አምላኪነት ደግሞ በዚያው ሰሞን “የተሳከረው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ውጤቶቹ” በሚለው የነብዩ ኃይሉ “ጽሑፍ” ይመለሳል፡፡ በአቶ ኀይቶም ከዓለም አንደኛ የሆንበት የዋጋ ንረት በአቶ ነብዩ ደግሞ በአይ.ኤም.ኤፍ የመረጃ ምንጭነት አንደኛ እንዳልሆንን ተረጋግጦ ይነበባል፡፡ ከዚህ በላይ መሳከር ከወዴት ይገኛል?

ስለአብዮታዊ ዴሞክራሲና ስለወቅቱ ሥርዓት አምርረው ከሚጽፉትና ስለዴሞክራሲና ነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ለሀገራችን ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ በማጉላት ከሚሞግቱት መካከል የፍትህ ዓምደኛው ሙሉነህ አያሌው አንዱ ናቸው፡፡ እኚህ ግለሰብ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም በኢትዮጵያ በተካሄደ ወቅት ፎረሙን መነሻ በማድረግ ስለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመረጃ የተደገፈ አስተያየት መስጠታቸው ይታወሳል።

“የአለም ኢኮኖሚ ፎረም በየጊዜው በሚያደርጋቸው የተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በዋነኛነት ከሚነሱት ነጥቦች መካከል አገራት ገበያቸውን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት በማድረግ የዜጎቻቸውን ህይወት በተለያየ መልኩ መለወጥ ይችላሉ፡፡ የውጭ ባለሀብቶች ለአገሪቱ የሥራ እድልን ከመፍጠራቸው

በተጨማሪ መንግሥት የሚያከናውናቸውን የልማት እቅዶች በመደገፍ የተሻለ ገበያ መር ምጣኔ ሀብታዊ አካባቢን መፍጠር ይችላሉ የሚለውን አመለካከት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በውይይቱ ለሚሳተፉ ፓናሊስቶች የመዝጊያ ሀሳብ እንዲሆን በእጅጉ ይጥራሉ፡፡”

“አዲስ አበባ ለዚህ ጉባዔ በዋናነት እንድትመረጥ ያደረጓት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አገሪቱ የአፍሪካ ህብረት ዋና መዲናና የዓለማችን ትልቅ የዲፕሎማቶች መቀመጫ መሆኗ ... ሁለተኛው የዘንድሮው ጉባኤ ሊነጋገርባቸው ካቀዳቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ግብርና በዋናነት የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢኮኖሚ የተመሰረተበት በመሆኑ ጉዳዩን በቅርበት ለማየት ተሞክሮዎችን ለመጎብኘት አመቺ ያደርገዋል፡፡” የሚለን ሙሉነህ በገደምዳሜውም ቢሆን ቢያንስ የሚወሰድ ምርጥ ተሞክሮ እንዳለን አረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል የዓለማችን ትልቋ የዲፕሎማቶች መቀመጫ ለመሆን ምን ብቃትና መስፈርት ማሟላት እንደሚያስፈልግ በልባችን ለምነገነዘበው ሁሉ ትልቅነታችንን እና ከእድገታችን የሚወሰድ ተሞክሮ ያለን በመሆኑ እድሉ እንዲሰጠን ስለማስቻሉ እንተማመናለን፡፡

የኒዮሊበራሉ ኃይል ተላላኪ የሆኑት የመድረክና የመድረኩ አባል የሆነው የአንድነት ስብስብ ቃል አቀባዮቻቸው ፍትህና ፍኖተ - ነፃነት ጋዜጦች ሳይቀሩ ጨዋታው በነሱ ሜዳ ላይ በሆነ ጊዜ ሁሉ ስለኒዮሊበራሉ ኃይል በመዘመር እንዳልተሟገቱ ሁሉ፤ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች (ፈረንጆች) ሽንጣቸውን ገትረው እንዳልተሟገቱ ሁሉ፤ ፈረንጆቹን በውስጥ ጉዳያችን አይመለከታችሁም ሲሻችሁ በሊማሊሞ ማቋረጥ ትችላላችሁ ያሉትን መሪ እንዳልኮነኑቱ ሁሉ ዛሬ ከድህነት እየወጣን ስለመሆኑና ስለእድገታችን ፈረንጆቹ እውቅና ቢሰጡን የነፃ ገበያና ሊበራላዊ ፍልስፍና የሚዋጋለትን የውጭ ኢንቨስትመንትና ንግድ መኮነናቸው ያስተዛዝባል፡፡

እንደኛ ሀገር ያሉ ተቃዋሚዎችና መሰሎቻቸው ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ስብሰባዎችን ሲቃወሙ ከራሳቸው አስተሳሰብና ፍልስፍና ጭምር ጋር እየተጋጩ ስለመሆናቸው ለማሰብ እንኳ አይፈልጉም፡፡

ለምሣሌ የሀብታም አገራት እርዳታ ያስፈልገናል፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ደግሞ ለዚህ ፍቱን ናቸው ሲሉን የከረሙት እነ ፍትህና የአንድነት ስብስቦች እንዲህ ዓይነት ፎረሞች በአገራችን ሲደረጉ የሀብታም ሀገራትን የፖሊሲ አቅጣጫ ብቻ የሚያንፀባርቅና የነሱ ተገዢ ለማድረግ ነው፡፡ መሬት ሊቀራመቱና የምግብ ዋስትናቸውን ሊያረጋግጡ ነው ሲሉ የማይገናኝ ሀሳቦችን በመሰንዘር በፊት የዘመሩበትን ግጥም ሙሾም ጭምር ሲያደርጉት ትዝብት ላይ ይጥለናል ብለው እንኳን አይሰጉም፡፡

ዳሩ ተሞዳሙዷል የተባለውና በፍትህና ፍኖተ ነፃነት ጋዜጦች የሚብጠለጠለው መሪ ለተሰጠን እውቅናና አድናቆት ሲል እንኳ ወደ ኋላ ሳይመለስ ያለ ምንም ማመንታት ማርሹን አሁንም

ያስገባው  ወደፊት ነው፡፡ ለተሰበሰቡት 700 ፈረንጆች “ as we grow, as we develop, as we become more sophisticated in our regulation we will liberalize” "እያደግን፣ እየተለወጥንና ተቋማት በሚገባ ደረጃ መራቀቅ ሲጀምሩ ያን ጊዜ ሊበራል እንሆናለን፡፡" በማለት እቅጩን ነግሯቸዋል፡፡ ታዲያ አንዴ እዚህ አንዴ እዚያ ጭቃ እየረገጠ መሳከሩን በግልጽ እያሳየን ያለው ማን ነው?

ነብዩ ስብሰባውን መቃወም አለባችሁ ያላቸውን የሀገሬ ተቃዋሚዎች በተመለከተ ተመስገን ደሣለኝ በግንቦት 3 ቀን 2004 ሀቲቱ የተሳከረውን የተቃውሞ ጎራ ከመራራ ጉዲና ባለ አምስት ገጽ ድርጅታዊ ፕሮግራም ጀምሮ እስከ ፕሮፌሰር በየነ የወንበር ፍሊጋና ሥልጣን ጥማት ድረስ ገላልጦ አሳይቶናል፡፡ ከእርሱ ጋር ለሚመቻመቹት ፓርቲዎች ደግሞ የፕሮግራም ሳይሆን የአመፅ አማራጮችን ካቀረበላቸው ጸሁፍ ማን እንደተሳከረ መረዳት ያስችለናል፡፡

የፍትህ ቋሚ አምደኛ ፕሮፌሰር መሥፍን በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅትን በመወከል የፊታውራሪነት ሚና ሲጫወቱ ከነበሩት ግለሰቦች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ከቅንጅት መፈራረስ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ሚናና ደካማ ጎን ለመናገር ባይደፍሩም ሌሎቹ አጋሮቻቸው ግን ፕሮፌሰሩ ለሥልጣን ያላቸውን ፍላጎትና አምባገነንነት በየምናምኑ ሲፅፉና ሲያፅፉ ደርሶን አንብበናል፡፡ ጉዳዩን ያነሳሁት የተሳከረው ማነው? ለሚለው ጥያቄ ጥሩ ምላሽ ስለሚሆነን ነው፡፡

የአብዮታዊ ዴሞክራሲንና ኢህአዴግን የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ጨምሮ ሥርዓቱን አምባገነን ሲሉ በመፈረጅ የምናውቃቸው ፕሮፌሰር መሥፍን ኢህአዴግ ከሥልጣኑ ወርዶ ለተቃዋሚው ማስረከብ እንዳለበት በተደጋጋሚ መወትወታቸውን አላቋረጡም፡፡ ሆኖም ቀደም ብዬ የጠቀስኩት የተመስገን ኑዛዜ አስደንብሯቸው ነው መሰል በፍትህ ጋዜጣ ግንቦት 10 ቀን 2004 እትም ላይ ሥልጣን ይረከቡ ያሏቸው ተቋዋሚዎች ስለመስከራቸው አብራርተዋል፡፡

“በ1997 መኢአድ፣ ኢዴፓ፣ ቀስተ ደመና የሚባሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ሆነው ቅንጅትን ፈጠሩ፣ ነገር ግን መኢአድን ከአቶ ኃይሉ ሻውል፣ ኢዴፓን ከአቶ ልደቱ አያሌው ህልውና ለመለየት በፍፁም የማይቻል ሆነ፣ ስለዚህም የቅንጅትን ህልውና ፈተና ውስጥ ከተቱትና ተበታተነ... ” ፕሮፌሰሩ ይቀጥላሉ

“በልደቱ የተጀመረው የቅንጅት መገነጣጠል በብርሀኑ ነጋና  በኃይሉ ሻውል ቀጥሎ ብርቱካን የምትመራው አንድነት ብቻውን ቀረ፡፡ በአንድነትም ውስጥ ገና ከመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ ጀምሮ ብርቱካን በመመረጥዋ ቅር ያላቸው አባሎች አኩርፈው ችግር ተፈጥሮ ነበር፡፡ ብርቱካን ስትታሰር ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በጉጉት ሲጠብቀው የነበረውን ወንበር አገኘና የአምባገነንነት አገዛዙን ከዶክተር ኃይሉ አርአያና ከአቶ ገብሩ አሥራት ድጋፍ መሰላሉን ሊወጣ ተመኘ፣ የወጣበት መሰላልም ወደቀ” ይሉናል ፕሮፌሰር፡፡ የተሳከረው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ከዚህ በላይ ምላሽ

ከየት አመጣለሁ፡፡ እዚህች ጋር መዘንጋት የሌለበት የኢንጂነር ግዛቸው መሰላል የወደቀው ይህን አስተያየት በሰጡት ፕሮፌሰር መሆኑ ነው፡፡

አሁንም እነዚሁ የተሳከሩቱ ስብስቦች በመድረክ ጥላ ሥር ሆነው ለራሳቸው ሳይግባቡ ስለ አወልያ፣ መጅሊሱ፣ ዋልድባ፣ ኮብል ስቶን እና የመሳሰሉትን አጀንዳዎች እያነሱ ሲሞግቱን እውን ተጨንቀው ነው? እውነት ለዚህ ሕዝብ አስበው ነው? የሚል ጥያቄ ማንሳት የሚችል ሰው የለም የሚል ንቀት አድሮባቸው እንደሆነ መጠራጠር የለብንም፡፡